የመደበኛ ወንጀል ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት በአብክመ ፍትሕ ቢሮ ሥር ከተደራጁ ዋና አላማ ፈፀማ የስራ ክፍሎች አንዱ ሲሆን የሙስና እና የኢኮኖሚ ወንጀሎችን ሳይጨምር በወንጀል ህጉና ሌሎች ልዩ ልዩ ህጎች የተመለከቱ ዘርፈ ብዙ የወንጀል ጉዳዮች የሚከታተል ላይ ን የወንጀል ምርመራን በመምራት በምርመራ መዝገቦች ላይ በባለቤትንነት የሚሰራ በአብክመ ፍትሕ ቢሮ በጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ዘርፍ ከተደራጁ የስራ ክፍሎች አንዱ ሲሆን የሚከተሉትን ዋና ዋና ተግባራት ያካናውናል።

- የወንጀል ምርመራ እንዲጀመር ወይም ተጨማሪ ምርመራ እንዲደረግ ወይም እንዲቋረጥ ወይም እንዲቀጥል በማድረግ የወንጀል ምርመራ ስራን በበላይነት ይመራል ያስተባብራል ይከታተላል ይቆጣጠራል፤ ይደግፋል፤
- ከበላይ አመራር ጋር በመመካከር የወንጀል ተጎጅወች ጠቋሚወችና ምስክሮች ተገቢውን ጥበቃና ከለላ እንዲያገኙ ያመቻቻል፣ ይከታተላል፣ የበቀል እርምጃ ስጋቶችን በህግ አግባብ ያግዳል፣ ያጣራል አፈጻጸሙን ይከታተላል፤
- በወንጀል ጉዳይ ክስ ይመሰርታል ተከታትሎ ያስወስናል ፣ያቀረበውን ክስ አንስቶ አስፈላጊውን ይወስናል የወንጀል ምርመራ መዝገብን ይዘጋል፤የክስ አይቀርብም ውሳኔ ይሰጣል
- በህግ መሰረት የጥፋተኝነት ድርድር ያደርጋል ፣ አማራጭ የመፍትሄ እርምጃ ይወስዳል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤
- በህግ መሰረት ቀዳሚ ምርመራ እንዲከናወን ጥእዛዝ ይሰጣል ፤
- ፍርድ ቤቶች በወንጀል ጉዳይ የሚሰጧቸው የእስር ፤የንብረት ውርስ የገንዘብ መቀጫና የኤዝግቢት ውሳኔዎችና ትዕዛዞች መፈፀማቸውንና መከበራቸውን ይከታተላል፣
- በወንጀል ምርመራ ሂደት የወንጀል ተጠርጣሪወች ዋስትናን ጨምሮ መብታቸው እንዲከበርና ኢሰብአዊ ድርጊት እንዳይፈፀም ይከታተላል ጥፋት የፈፀሙ አካላት በህግ እንዲጠየቁ ያደርጋል ፤
- ከወንጀል ምርመራ ጋር የሚያዙ ኤዝግቢቶች አስተዳደር አያያዝና አቀማመጥ ላይ እንደአስፈላጊነቱ በራሱ ወይም ፍርድ ቤት በማቅረብ ውሳኔ እንዲያገኝ ያደርጋል፤አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፤
- ወንጀሎችን ለመከላከልና ውጤታማ ለማድረግ የንቃተ ሕግ ትምህርት ይሰጣል ጥናቶችን ያደርጋል፣ ፤የስራክፍሉ ለማሻሻል የሚረዱ የስልጠና ፅሁፎችን ያዘጋጃል ስልጠና ይሰጣል፤

- ከወንጀል ጉዳዮች ጋር በተያያዘ ከቢሮ ኃላፊው ወይም ዘርፉን ከሚመራው ምክትል ቢሮ ኃላፊ ተለይተው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፤

- የመደበኛ ወንጀል ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ለወንጀል ጉዳይ ዳይሬክቶሬቶች በወል ከተሰጡ ተግባር እና ኃላፊነቶች እንደተጠበቁ ሆነው ፤በኢፌዴሪ የወንጀል ህግ የተመለከቱ የወንጀል ጉዳዮች ፤ እና በሌሎች ህጎች

**በተመለከቱ የወንጀል ጉዳዮች ላይ ተግባርና ኃላፊነት ያለው ሲሆን የኢኮኖሚ ወንጀል ጉዳዮች፣የሙስና ወንጀሎች እና ፍትህ ሚኒስትር ውክልና ያልሰጠባቸው የወንጀል ጉዳዮችን አያካትትም**

ዳይሬክቶሬቱ የሚታዩ የወንጀል ጉዳዮች ፡-

- ❖ **፤የሙስና የኢኮኖሚ ብሔር ተኮርና ሀይማኖት ተኮር ወንጀሎጭ ውጭ በኢፌዴሪ የወንጀል ህግ የተመለከቱ ሁሉም የወንጀል ጉዳዮች፤**

1. በኢትዮጵያ የወንጀል ሕግ እና በፀረ-ሽብርተኝነት አዋጅ ላይ የሽብር ወንጀሎች ተብለው የተዘረዘሩ ወንጀሎች፣
2. በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብ (Money Laundering) እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳት (Financing of Terrorism) ጋር ተያይዞ የሚፈፀሙ ወንጀሎች (አዋጅ ቁጥር 780/2005
3. የኮምፒዩተር ወንጀል አዋጅ ቁጥር 958/2008 ን በመተላለፍ የሚፈጸሙ ወንጀሎች፣
4. የጦር መሳሪያ አስተዳደር እና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 1177/2012 ን በመተላለፍ የሚፈጸሙ ወንጀሎች ፣
5. በሰው የመነገድ እና ሰውን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር አዋጅ ቁጥር 1178/2012 ስር የተመለከቱ የወንጀል ጉዳዮች ፣
6. ከቴሌኮም ማጭበርበር ጋር በተያያዘ የሚፈፀሙ ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 761/2004፣
7. በዋና ዋና የመሠረተ ልማት አውታሮች ላይ የሚፈፀሙና አዋጅ ቁጥር 464/1997 ስር የተመለከቱ ወንጀሎች (ለምሳሌ በኤሌትሪክ/በኃይል ማመንጪያና ማስተላለፊያ/፣ በቴሌ ኮምዩኒኬሽን፣ በባቡር…)፣
8. የጥላቻ ንግግር እና የሀሰት መረጃ ማሰራጨት የሚከለክለውን አዋጅ በመተላለፍ የሚፈጸሙ ወንጀሎች
9. የሚዲያ እና ፕሬስ ሕግን በመጣስ የሚፈፀሙ ወንጀሎች፣ ከመገናኛ ብዙሀን እና መረጃ ነጻነት አዋጅ ጋር ተያይዞ በሰው ክብር እና መልካም ስም ላይ የሚፈጸሙ ሆነው በዐቃቤ ሕግ ክስ ሊቀርብባቸው የሚገባ ወንጀሎች፤
10. በተደራጁ እና ድንበር ተሻጋሪ ወንጀሎች የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብ እና ስለመርዳት፣

11. የደን ጥበቃ አዋጅን በመተላለፍ የሚፈጸም ወንጀል (አዋጅ ቁጥር 542/1999)፤

12. የአካባቢ ጥበቃ አዋጅን በመተላለፍ የሚፈጸም ወንጀል (አዋጅ ቁጥር 299/1995፣ 300/1995)፤

13. የተሽከርካሪዎች የሶስተኛ ወገን መድን ሽፋንን ለመደንገግ የወጣውን አዋጅ በመተላለፍ የሚፈጸም ወንጀል፣

14. የወንጀል ጠቋሚዎችና ምስክሮች ጥበቃ አዋጅን በመተላለፍ የሚፈጸም ወንጀል (አዋጅ ቁጥር 699/2002) እና በሌሎች አዋጆች የተመለከቱ ልዩ ልዩ ወንጀሎችን ይመለከታል፤

15. የቅጂ እና ተዛማች መብት ጥሰቶች፣ አነስተኛ ፈጠራ መብት ጥሰቶች፣

16. በሌሎች ህጎች የወጡ የሙስና እና የኢኮኖሚ ወንጀል ያልሆኑ ሁሉም አይነት ወንጀሎች፣

17. በሌሎች የወንጀል ጉዳዮች ዐቃቤ ሕግ የስራ ክፍሎች ከሚታዩ ሌሎች የወንጀል ጉዳዮች ጋር የተደራጁ እና ድንበር ተሻጋሪ ወንጀል ጉዳዮች በተደራቢነት የሚገኝ በሚሆንበት ጊዜ ከፍተኛ ቅጣት የሚያስከትለው ጉዳይ በመደበኛ ወንጀል ዳይሬክቶሬት የሚታይ ከሆነ ሌሎችም ተጣምተረው አንድ ላይ ይታያል።